# ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)
## 23 ኛ ሳምንት
## እረኛው ዳዊት

**ዓላማ**

- ስለ ንጉሥ ዳዊት የልጅነት ዘመን መማር፡፡

**ምንባብ**

- 1ኛ ሳሙ.17÷34-36

**መግቢያ**

- ዳዊት የአይሁድና የመላው እስራኤል ንጉሥ ነበር፡፡
- እምነትና ትህትና ስለነበረውም እግዚአብሔር ንጉሥ እንዲሆን መረጠው፤
- በዛሬው ትምህርታችንም የዳዊትን የልጅነት ዘመንና ለንግሥና መመረጡን እንማራለን፡፡

**ትምህርቱ**

- ሕፃኑ ዳዊት የአባቶቹን በጎች የሚጠብቅ መልከ መልካም ልጅ ነበር፡፡ በጎቹን ይወዳቸዋል፡፡ በዋሽንት ያዜምላቸዋል… በጎቹም በዙሪያው ይሰበሰባሉ፡፡
- ዳዊት በጎቹን የሚጠብቅበት ዘንግም ነበረው፡፡ለበጎቹም ይጠነቀቃል፡፡እነርሱን ለመጠበቅም ከአንበሳና ድብ ጋር ይታገላል፡፡
- ዳዊት ሁሌም የእግዚአብሔርን ስም ይጠራል፤የአባቱን በጎች ለመጠበቅ ከመውጣቱም በፊት ይጸልያል፣ ይዘምራልም፡፡
- ከአንበሳና ድብ በጎቹን የሚያድኑበትን ኃይልና ችሎታ እንደሰጠው ያውቅና ያምን ነበርና ሁሌም እግዚአብሔርን ያመሰግናል፡፡

**ለንጉሥነት መመረጡ**

- ሳሙኤል የተባለ ነቢይ ነበር፡፡ *ልጆች ነቢይ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?* ነቢይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መልእክት እንዲነግር የሚልከው ነው ፡፡
- አንድ ቀን ሳሙኤል ቀንዱን በዘይት ሞልቶ እሴይ ወደ ተባለ ሰው ቤት እንዲሄድ ነገረው፡፡ ከእሴይ ልጆችም ለንግሥና የመረጠውን እንዲቀባው አዘዘው፡፡
- እግዚአብሔር እንደነገረውም ሳሙኤል ወደ እሴይ ሄደ፡፡ እሴይና ጎረቤቶቹ የእግዚአብሔር ነቢይ ስለሆነ የእግዚአብሔር መልእክት እንዳለው አውቀው፡፡ለምን? እንደመጣ ጠየቁት ሳሙኤልም መሥዋዕት ለማቅረብ እንደመጣ ራሳቸውን እንዲያነጹና ለመስዋዕት ሥርዓቱ እንዲዘጋጁ ነገራቸው፡፡
- ወደ እሴይ ቤት ከገባ በኋላም የመጀመሪያው የእሴይ ልጅ ሲመጣም ሳሙኤል እግዚአብሔር ለንግሥና የመረጠው ይሄ ይሆናል አለ፡፡እግዚአብሔር ግን እርሱን እንዳልመረጠና ሰው ፊትን ቢያይም እርሱ ግን ልብን እንደሚያይ ነገረው፡፡
- እሴይ ልጆቹን ሁሉ በሳሙኤል ፊት ተራ በተራ እያመጣ አቆመ፡፡ እግዚአብሔር ግን ሁሉንም አልመረጠም፡፡ በመጨረሻም የቀረ ልጅ የለም? ብሎ ሳሙኤል እሴይን ጠየቀው፡፡ የመጨረሻው ልጅ እንዳለና በጎች እየጠበቀ መሆኑንም ነገረው፡፡
- ሳሙኤልም ፈጥኖ እንዲያመጣው ነገረው፤የመጨረሻው ልጅ ዳዊት ሲመጣም ብሩህ፣ መልከ መልካምና ግርማ ሞገስ ያለው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ለሳሙኤል ***"ይህ ነውና ተነሥተህ ቀባው"*** አለ፡፡
- ዳዊት በወንድሞቹ መካከል ተቀባ የእግዚአብሔርም መንፈስ ከዚያን ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ፡፡

**ደብረ ዘይት**

- ልጆች ይህ አሁን የምንጀምረው የዐቢይ ጾም ሳምንት ስንተኛው ሳምንት ነው?
  - ✓ 5ኛው ሳምንት ነው፡፡
- ምን ተብሎ እንደሚጠራ ታውቃላችሁ?
  - ✓ አዎን ደብረዘይት ይባላል፡፡
- ደብረ ዘይት ማለት ምን ማለት ?
  - ✓ የዘይት ተራራማለት ነው፡፡ዘይት የሚያወጡ የወይራ ዛፎች በብዛት ስለነበሩት  ደብረዘይት ተብሎል፡፡
- ለምን እናከብረዋለን ?
  - ✓ ጌታችን በዚህ ተራራ ያስተማረው ትምህርት እና ዳግሞ ምጽአቱን ለማሰብ፡፡
  - ✓ የዐቢይ ጾም ግማሹ /እኩለ ጾምም/ ነው፡፡

**ጥያቄዎች**

1.ዳዊት አባቱን ያገለግል የነበረው እንዴት ነው?
2. ዘንግ ይይዝ የነበረውስ ለምንድነው ?
3. ከድብና አንበሳ ጋር የሚታገልበትን ኃይል ማን ሰጠው?
4. ለምን ነበር የሚታገለውስ?
5.ነቢይ ምንድነው?
6. ወደ እሴይ ቤት የተላከው ነቢይ ማንነው?
7. ነቢዩ በእሴይ ቤት ለንግሥና የሚሆነውን ሲመርጥ  ዳዊት ምን ያደርግ ነበር?

**መዝሙር**

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው (2)
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው (2) አምላኬ መመኪያዬ ነው (2)

# David Annointed



ይቆየን፡፡